Bless your Pastor
መንገዶች

# እነዚህ ጥቂት ዓመታት ለመጋቢዎች አስቸጋሪ ዓመታት ነበሩ። አሁን ላይ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለመጋቢዎና ለቤተ ክርስቲያን ሰራተኞች ለማሳየትና ለማካፈል እጅግ ቀላል ሆኗል።

ይህንን ገፅ በአማርኛ ለማግኘት **BlessYourPastor.org/123amharic** የሚለውን ይጫኑ ወይም የእንግሊዘኛውን ገፅ ለማግኘት ደግሞ **BlessYourPastor.org/123** የሚለውን ይጎብኙ

**1 መምረጥ** በቅድሚያ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ያሉ ሁሉም ቤተሰቦች ከ50ዎቹ መንገዶች ዝርዝር ውስጥ አንዱን መቼ እንደሚያካፍሉ ይምረጡ። 50ዎቹ መንገዶች ሁሉም ሰው የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዲያሳይና እንዲያካፍል ይረዳሉ። የቤተ ክርስቲያናችሁ መሪዎች በአምልኮ አገልግሎት፣ በቤተ ክርስትያን ማስታወቂያ፣ በጋዜጣ፣ በኢሜል ወይም በፖስታ ዝርዝሩን ከቤተ ክርስትያን አባላት ጋር ለመጋራት ዝግጅት ማድረግ ይችላሉ።

**2 መሰብሰብ** እንደሚታወቀው የጥቅምት ወር በአሜሪካ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የመጋቢዎች ወር ተብሎ ይከበራል እርስዎም በዚህ ወር ከእኛ ጋር አብረው እንዲያከብሩ እየጋበዝን በዚህ ወር፣ ደግሞም በኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል (ገና) ወይም የፋሲካ ወቅት ልዩ የምስጋና ስጦታ ከጉባኤው ወይም በሽማግሌዎች የተፈቀደ የመጋቢና የቤተ ክርስቲያን ሰራተኞች ስጦታ መሰብሰብ።

**3 አክብሮትን ማሳየት** ለመጋቢዎና ለቤተ ክርስቲያኑ ሰራተኞች ከሚከተሉት በአንዱ ወይም በብዙ መንገዶች ምስጋናዎን ይግለጡ፡ ፖስት ካርዶችን/ማስታወሻዎችን/የስጦታ ካርዶችን መሰብሰብ፤ በቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞች ላይ አክብሮትን መግለፅ እንዲሁም መፀለይ፤ የምስጋና ማዕድ ፕሮግራም በማዘጋጀት፤ ልጆች ስዕሎችን እንዲስሉ ወይም ማስታወሻ እንዲጽፉ በመጠየቅ እና/ወይም ምዕመናን ለምን መጋቢያቸውን እንደሚያደንቁ በመግለፅ ምስጋናቸውን በማህበራዊ ሚዲያ ላይ እንዲለጥፉ ማበረታታት።

## $200 የስጦታ ካርዶች ለዋና መጋቢዎች እንዲሁም የመዝናኛና የእረፍት ስጦታዎች

ሁሉንም 3 ደረጃዎች ላጠናቀቁና 100 ዶላር ወይም ከዚያ በላይ የምስጋና መባ ለሚሰበስቡ ለመጀመሪያ ጊዜ ተሳታፊ አብያተ ክርስቲያናት ዋና መጋቢዎች በስጦታ የተበረከተ የ200 ዶላር የአማዞን የስጦታ ካርድ በኢሜይል እናበረክታለን። ለሁሉም ተሳታፊ አብያተ ክርስቲያናት መጋዎች የነጻና የዋጋ ቅናሽ ያለው የመዝናኛና የዕረፍት ጊዜ እድሎች እንዲያገኙ ይደረጋል።

ቀጣዩ ደረጃ **BlessYourPastor.org/gifts** ገፅ ላይ ያለውን ቅጽ መሙላት ነው

ከኦገስት *1* እስከ ጃንዋሪ *15, 2023* በኦንላይን ለሚያመለክቱ በዩኤስኤ/ካናዳ ውስጥ ላሉ ለመጀመሪያዎቹ *2,000* አብያተ ክርስቲያናት የተገደበ ዕድል ነው። የስጦታ ካርዶች ወደ ሌላ ሀገር መላክ አይችሉም። ለእያንዳንዱ አዲስ ቤተ ክርስቲያን አንድ የ*200* ዶላር የስጦታ ካርድ ብቻ ይላካል።

## ተጨማሪ መርጃዎች

- የገንዘብ አስተዳደር ትክክለኝነትና የልግስና ስልጠና ቪዲዮዎች ለመጋቢዎችና ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች NAEfinancialhealth.org/trainingvideos
- የገንዘብ አስተዳደርዎን ይባርኩ ቪዲዮ ኮርስ የገንዘብ አስተዳደራቸውን ማሻሻል ለሚፈልጉ ግለሰቦችና ጥንዶች ነፃ፣ ቀላልና በበይነመረብ የሚሰጡ የስልጠና ቪዲዮዎችንና ምርጥ የተሞክሮ መርጃዎችን ያግኙ BlessYourFinances.org
- የመጋቢዎችና የቤተ ክርስቲያን ሰራተኞች የደሞዝ ጥናት BlessYourPastor.org/salaryresearch

*መጋቢዎን ይባርኩ በብሔራዊ የወንጌላውያን ማህበር የተዘጋጀ ንቅናቄና ሀገር አቀፍ የሚዲያ ዘመቻ ሲሆን ይህም ክርስቲያኖችንና አብያተ ክርስቲያናት ለመጋቢዎቻቸውና ለቤተ ክርስቲያን ሰራተኞች የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዲያሳዩና እንዲያካፍሉ የሚያበረታታና የሚያስታጥቅ ነው። እ.ኤ.አ. በ2019-2021፣ በዩናይትድ ስቴትስ/ካናዳ/ፖርታ ሪኮ ላሉ 2,500 ዋና መጋቢዎች የአማዞን የስጦታ ካርዶችን ሰጥቷል እንዲሁም ደግሞ በሺዎች ለሚቆጠሩ አብያተ ክርስቲያናት የመጋቢዎን ይባርኩ ግብዓቶችን ሰጥቷል። ይህ እንቅስቃሴ በብዙ ብሔራዊ ቤተ እምነቶች፣ ማህበራት፣ የንግድ ድርጅቶች፣ የአገልግሎት ተቋማት፣ ብሮድካስተሮችና አታሚዎች ስፖንሰር የተደረገ ነው። ለበለጠ መረጃ **BlessYourPastor.org.** ይጎብኙ

ከ50 በላይ የፈጠራ መንገዶች

Bless your Pastor and Staff

> እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ በእናንተ መካከል በትጋት የሚሠሩትን፣ በጌታም የበላዮቻችሁና መካሪዎቻችሁ የሆኑትን እንድታከብሯቸው እንለምናችኋለን፤
> 1 ተሰሎንቄ 5:12 አመት

## በታማኝነት ጸልዩ

መጋቢዎንና የቤተ ክርስቲያን ሰራተኞችን ለመርዳት እጅጉን የተሻለው መንገድ ለሚከተሉት ጉዳዮች መጸለይ ነው፡-

- ከእግዚአብሔር ጋር እንዲቀራረቡ
- የጋብቻ ፍቅርና አንድነት እንዲኖራቸው
- መንፈሳዊ ጥበቃ እንዲደረግላቸው
- መለኮታዊ መመሪያ እንዲሰጣቸው
- ስሜታዊ እና አካላዊ ደህንነት እንዲኖራቸው
- የወላጅነት ችሎታዎች እንዲሰጧቸው
- እውነተኛ ጓደኝነት እንዲኖራቸው
- የገንዘብ አቅርቦቶች እንዲኖራቸው
- የዕለት ተዕለት ጥበብ እንዲሰጣቸው
- የግል ማበረታቻ እንዲያገኙ
- ጠቃሚ አማካሪዎች እንዲኖሯቸው
- ውጤታማ አገልግሎት እንዲኖራቸው
- ውጤታማ የጊዜ አጠቃቀም እንዲኖራቸው
- ጥራት ያለው የጥናትና የጸሎት ጊዜያት እንዲኖራቸው

## ፍቅር

- እግዚአብሔር እርስዎን ለመባረክ፣ ለመርዳትና እርሱን እንዲከተሉ ለማስተማር እንዴት እነርሱን እንደሚጠቀምባቸው ያሳውቋቸው።
- የልደት ቀኖቻቸውና አመታዊ በዓሎቻቸውን በካርድ፣ በስጦታ ወይም በማህበራዊ ሚዲያ ልጥፍ ያስታውሱ።
- ለጥንካሬዎቻቸው አድናቆትዎን ያሳዩ ለድክመታቸው ደግሞ ርህራሄን ያሳዩ።

## ነፃነት

- የትዳር አጋሮቻቸው እራሳቸውን እንዲሆኑና በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የራሳቸውን ቦታ እንዲያገኙ ነፃነትን ይስጡ።
- ልጆቻቸው "ልጆች ይሁኑ፣" ያስቡላቸው እንዲሁም ይጸልዩላቸው።

## ምግብ፣ ህብረትና መዝናኛ

- ምግቦችን ያዘጋጁላቸው (ስለሚወዷቸው ምግቦች ወይም ማዘጋጀት ስለሌለባችሁ የተወሰኑ ምግቦች ይጠይቁ)።
- ለሬስቶራንቶች፣ ለፈጣን ምግብ ቤቶች ወይም ለቡና መሸጫ ሱቆች የስጦታ ካርዶችን ይስጧቸው።
- ከጓሮ አትክልትዎ፣ ከአትክልት ስፍራዎ፣ ከአደንዎ ወይም ከአሳ ማጥመጃ ጉዞዎ ያገኙትን ያካፍሏቸው።
- እነርሱንና ቤተሰቦቻቸውን ወደ ቤትዎ ወይም ሬስቶራንት የመዓድ ግብዣ ይጋብዟቸው።
- እነርሱንና ቤተሰቦቻቸውን ወደ ዓሳ ማጥመድ፣ የመርከብ ጉዞ፣ ካምፕ፣ አደን፣ ጂም፣ ኮንሰርቶች፣ ጨዋታዎች ወይም የስፖርት ዝግጅቶች እንዲሄዱ ይጋብዟቸው። የተወሰነውን ወይም ሁሉንም ወጪዎች ለመሸፈን ጥያቄ ያቅርቡ።
- መጋቢዎንና የቤተ ክርስቲያን ሰራተኞችን የስፖርት፣ የኮንሰርት ወይም የልዩ ፕሮግራም ትኬቶችን ይግዙላቸው።
- የዕረፍት ጊዜ ቤት፣ የመዝናኛ ተሽከርካሪ ወይም የካምፕ ጉዞ ቁሳቁስ ካለዎት እንዲጠቀሙበት ይጋብዙ።
- ለኮንፈረንስ፣ ለዕረፍት፣ ለተልዕኮ ጉዞዎች ወይም ለበዓል ጉዞ የሚያገለግሉ ተደጋጋሚ በራሪ ማይልሶችን ያጋሩ።
- ለበዓል የቤተሰብ ጉዞ ወይም የዕረፍት ጊዜ የሚጠቀሙበት አስተማማኝ ተሽከርካሪዎን እንዲጠቀሙ ያቅርቡ።

## በነጻነት ያካፍሉ

ከሚከተሉት ዝርዝሮች ውስጥ በመረጡት ለመርዳት ችሎታዎንና ጊዜዎን ያካፍሉ;

- ልጆችን መንከባከብና መጠበቅ
- የመኪና ጥገና
- የቤት ጥገናና ተያያዥ ፕሮጀክቶች
- የግድግዳ ወረቀት መለጠፍ፣ ማስጌጥና መቀባት
- የፀጉር ማስተካከልና የውበት ስራዎች
- የጤና፣ የጥርስና የካይሮፕራክቲክ እንክብካቤ
- የመናፈሻ ስፍራና የአትክልት እንክብካቤ
- የሕግ፣ የንብረትና የገንዘብ አስተዳደር አገልግሎቶች
- ልጆች ማስጠናት ወይም የልጆች ትምህርት

ካስፈለገና መጋቢው ወይም የቤተ ክርስቲያኑ ሰራተኞች መሸፈን የሚገባቸው የኪስ ወጪዎች ካሉ (ለምሳሌ የመኪና ጥገና ክፍሎችን ወይም ለቤት ጥገና ወጪዎች) አስቀድመው ይነጋገሩ።

## የገንዘብ አስተዳደር

ለቤተ ክርስቲያንዎ በታማኝነት ይስጡ፣ እንዲያ ቢያደርጉ መጋቢዎና የቤተ ክርስቲያኑ ሰራተኞች በቂ ደሞዝ ይከፈላቸዋል። ከቤተ ክርስቲያን ደሞዝ ባሻገር፣ ጌታ አንዳንድ ግለሰቦች ከሚከተሉት ነገሮች ውስጥ በአንዱ በግል እንዲያግዙ ሊያሳስብዎ ይችላል፡-

- መጋቢያችሁንና የቤተ ክርስቲያን ሰራተኞችን የመባረክ መባ
- የጋብቻ መዝናኛ ወጪዎች
- የክርስቲያን ካምፕ ጉዞ ክፍያዎችን
- ወደ ትምህርት ቤት መመለስ ክፍያ፣ ልብስ ወይም ቁሳቁስ ወጪ
- የልጆች የኮሌጅ ትምህርት ክፍያ
- የሚሽን ጉዞዎች ወጪ
- ትምህርቶች ወይም የጥናት አገልግሎቶች
- የቤተሰብ ወይም የጥንዶች የእረፍት ጊዜ
- የመጋቢዎች ኮንፈረንስ፣ ሴሚናር ወይም ስልጠና
- የሴሚናሪ ኮርሶች ወይም ሳባቲካል
- የተማሪ ብድር ዕዳ
- የጡረታ ቁጠባዎች
- የሕክምና ወጪዎች

## ለሌሎች በጎ ማድረግ

ብዙ ሰዎች "ለሌሎች በጎ ስለማድረግ/ pay it forward" ሰምተዋል። ከአሁን በኋላ የማይጠቀሙባቸውን ወይም የማይፈልጓቸውን ንብረቶች በመስጠት ለሌሎች በጎ ማድረግ እንደሚችሉ ያውቃሉ? ሊሆኑ የሚችሉ እቃዎች የቤት እቃዎች፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ልብሶች፣ የስፖርት መሳሪያዎች ወይም ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ናቸው። ሊያበረክቷቸው የሚችሏቸው እቃዎች በእርግጥ በመጋቢው ወይም በቤተ ክርስቲያኑ ሰራተኞች የሚፈለጉና የሚያስፈልጉ መሆናቸውን ይጠይቁ። እንዲሁም በጥሩ ሁኔታ ላይ መሆናቸውንና ብዙ ወጪ የሚያስወጣ ጥገና እንደማያስፈልጋቸው እርግጠኛ ይሁኑ።

ማስታወሻ፡ እባክዎን መጋቢዎ ወይም የቤተ ክርስቲያኑ ሰራተኞች የሚያቀርቡትን ማንኛውንም ነገር ውድቅ ቢያደርጉ በደስታ ለመቀበል ይዘጋጁ። በተጨማሪም እዚህ ላይ የተገለጹት አብዛኛዎቹ እቃዎች ለሰጪው በተለምዶ ቀረጥ የሚቀነሱ አይደሉም ነገር ግን እግዚአብሔር ለሰጠን ነገሮች ካለን ምስጋና የተነሣ የሚሰጥ መሆኑን አስተውሉ።

ከBlessYourPastor.org የማባዛት ፍቃድ ተሰጥቷል

## የ50 መንገዶችን ዝርዝርና የመጋቢዎች የአድናቆት መባ መጠይቅ ለማከፋፈል የሚያግዝ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ደብዳቤ ወይም የኢሜል ቅንብር (የተዘጋጀ ጽሑፍ)

ውድ የቤተ ክርስቲያናችን አባል፡

ጌታ ጉባኤያችንን በመልካም ለማገልገል ጠንክሮ የሚሰራ ድንቅ መጋቢ ሰጥቶናል።

መጽሐፍ ቅዱስ በ1 ተሰሎንቄ 5:12 ላይ “እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ በእናንተ መካከል በትጋት የሚሠሩትን፣ በጌታም የበላዮቻችሁና መካሪዎቻችሁ የሆኑትን እንድታከብሯቸው እንለምናችኋለን” በማለት ያዘናል። ገላትያ 6:6 ላይ ደግሞ እንዲህ ይላል “ማንም ቃሉንየሚማር፣ መልካም የሆነውንነገር ሁሉ ከመምህሩጋር ይካፈል።” ይህንን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የበረከት ጥሪ ለመፈፀምና መጋቢ [የመጋቢውን ስም ያስገቡ] ለመባረክ ቤተ ክርስቲያናችን መጋቢዎን ይባርኩ የሚለው አገር አቀፍ እንቅስቃሴ ውስጥ ትሳተፋለች።

ስለዚህ መጋቢያችሁን ለመባረክ 50 የፈጠራ መንገዶች ዝርዝርን በጸሎት እንድታነቡ እንጋብዛለን። እግዚአብሔር ሁላችንም ለመጋቢያችንና ለቤተ ክርስቲያን ለሰራተኞች ያለንን አድናቆትና እንክብካቤ ለማሳየት እርሱ የሰጠንን ጊዜያችንን፣ ተሰጥዖአችንን፣ ሀብታችንንና መልካም ነገሮችን እንድናካፍል እንዲረዳን ምኞታችን ነው።

ፍቃደኛ ለሆናችሁና አቅም ላላችሁ አባላት በዚህ አጋጣሚ መጋቢያችንን በልዩ ስጦታ ለመባረክ እንወዳለን። በዚህ ደብዳቤ፣ መጋቢዎን ይባርኩ የሚል ፖስታ አቅርበናል። በማንኛውም ጊዜ ማለትም [ ቀን ያስገቡ]  መጋቢዎን ይባርኩ ዕለተ እሁድ ላይ ወይም ከዚያ በፊት ስጦታዎን ይላኩ ወይም በበይነመረብ በሚከተለው አድራሻ [አድራሻ ያስገቡ] ይስጡ። በፖስታው ውስጥ ለመጋቢዎ ልዩ የምስጋና ማስታወሻ ማካተት ይችላሉ።

እንወድሃለን ደግሞም የቤተ ክርስቲያናችን ቤተሰብ አካል ስለሆንክ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። በልግስናና ልግስና በማድረግ ስናድግ እግዚአብሔር በዘመናችን ሁሉ ምን እንደሚሰራ ለማየት በጉጉት እንጠባበቃለን።

በክርስቶስ የእናንተ
[የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ስም ያስገቡ]

## የሚሰበሰበው መባ ለመጋቢውና ለቤተ ክርስትያን ሰራተኞች ከሆነ ጥቅም ላይ የሚውል ቅንብር (የተዘጋጀ ጽሑፍ)

ውድ የቤተ ክርስቲያናችን አባል፡

ጌታ ጉባኤያችንን በመልካም ለማገልገል ጠንክረው የሚሰሩ ድንቅ መጋቢና የቤተ ክርስትያን ሰራተኞችን ሰጥቶናል።

መጽሐፍ ቅዱስ በ1 ተሰሎንቄ 5:12 ላይ “እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ በእናንተ መካከል በትጋት የሚሠሩትን፣ በጌታም የበላዮቻችሁና መካሪዎቻችሁ የሆኑትን እንድታከብሯቸው እንለምናችኋለን” በማለት ያዘናል። ገላትያ 6:6 ላይ ደግሞ እንዲህ ይላል “ማንም ቃሉንየሚማር፣ መልካም የሆነውንነገር ሁሉ ከመምህሩጋር ይካፈል።” ይህንን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የበረከት ጥሪ ለመፈፀምና መጋቢያችንንና የቤተ ክርስቲያን ሰራተኞችን ለመባረክ ቤተ ክርስቲያናችን መጋቢዎን ይባርኩ የሚለው አገር አቀፍ እንቅስቃሴ ውስጥ ትሳተፋለች።

ስለዚህ መጋቢያችሁንና የቤተ ክርስቲያን ሰራተኞችን ለመባረክ 50 የፈጠራ መንገዶች ዝርዝርን በጸሎት እንድታነቡ እንጋብዛለን። እግዚአብሔር ሁላችንም ለመጋቢያችንና ለቤተ ክርስቲያን ለሰራተኞች ያለንን አድናቆትና እንክብካቤ ለማሳየት እርሱ የሰጠንን ጊዜያችንን፣ ተሰጥዖአችንን፣ ሀብታችንንና መልካም ነገሮችን እንድናካፍል እንዲረዳን ምኞታችን ነው።

ፍቃደኛ ለሆናችሁና አቅም ላላችሁ አባላት በዚህ አጋጣሚ መጋቢያችንንና የቤተ ክርስቲያን ሰራተኞችን በልዩ ስጦታ ለመባረክ እንወዳለን። በዚህ ደብዳቤ፣ መጋቢዎንና የቤተ ክርስቲያን ሰራተኞችን ይባርኩ የሚል ፖስታ አቅርበናል። በማንኛውም ጊዜ ማለትም [ቀንያስገቡ] መጋቢዎንና የቤተ ክርስቲያን ሰራተኞችን ይባርኩ ዕለተ እሁድ ላይ ወይም ከዚያ በፊት ስጦታዎን ይላኩ ወይም በበይነመረብ በሚከተለው አድራሻ [አድራሻ ያስገቡ] ይስጡ። በፖስታው ውስጥ ለመጋቢዎ ወይም ለፈለጉት የቤተ ክርስቲያን ሰራተኛ ልዩ የምስጋና ማስታወሻ ማካተት ይችላሉ።

እንወዳችኋለን ደግሞም የቤተ ክርስቲያናችን ቤተሰብ አካል ስለሆናችሁ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። በልግስናና ልግስና በማድረግ ስናድግ እግዚአብሔር በዘመናችን ሁሉ ምንእንደሚሰራ ለማየት በጉጉት እንጠባበቃለን።

በክርስቶስ የእናንተ
[የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ስም ያስገቡ]

## መጋቢዎን ይባርኩ ሎጎና ግራፊክስ

ይህንን ዘመቻ ለማስተዋወቅ ቤተ ክርስቲያናችሁ ልትጠቀምባቸው የምትችላቸውን የመጋቢዎን ይባርኩ ሎጎና ግራፊክስ ለማግኘት እባክዎት ይህንን ይጫኑ።
blessyourpastor.org/dropboxmaterials